# እውነትም የጨለማና የቆሻሻ ጊዜ ...
# (የኢትዮጵያ እና ኤርትራ ጉዳይ)

ይህን ፅሁል ለመፃፍ ያነሳሳኝ ነገር ወደ ኤርትራ የአንድ ቀን ደርሶ መልስ ስላደረግኩ ባየሁት ነገር ተነሳስቼ ነው፡፡ አሁን በኢትዮጵያና ኤርትራ የተፈጠረው ሰላም፣ በተለይ በዛላንበሳ በተሎኮሰው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ዕድል ተጠቅሞ በርካታ የሁለቱም አገሮች ዜጎች በመኪናዎቻቸው ድንበር እያቋረጡ መግባት ከጀመሩ ሳምንት ሆኖዋል፡፡ ለ20 ዓመት ይቅር እና መኪኖች፣ ከወታደር ውጭ አንድም ሰው አስተናግደው የማያውቁት የመኪና መንገዶች፣ አሁን 24 ሰዓት በመኪኖች ተጨናንቆ ሲታይ  ልዩ የደስታ ስሜት ይሰማሀል፡፡ እኔም ይህን የደስታ ስሜት ተሰምቶኝ ከነ ስጋቴ ትላንት ኤርትራ ውስጥ ገብቼ ቶሎ ተመለስኩኝ፡፡

የምን ስጋት? የሚል ጥያቄ እንደሚጭርባቹ ይገባኛል፤

ምንም እንኳ የኢትዮ ኤርትራ የሰላም እንቅስቃሴ ከተጀመረ ወራት ያስቆጠረ ቢሆንም በሰላም ሂደቱ ይታዩ የነበሩ የሁለቱም መሪዎች (የጠ/ሚ ዶ/ር አብአ አሕመድ እና የፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ) እንቅስቃሴዎች ብዙ የማይመቹ ነገሮች ነበሩት፡፡ በተለይ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ በአሜሪካ ጉብኝታቸው ላይ ለዳያስፖራው ካደረጓቸው ንግግሮች አንዱ "ባለፉት 27 ዓመታት የጨለማና የቆሻሻ ጊዜ ነበሩ" የሚል እና ሁለተኛው ደግሞ "የኢትዮ-ኤርትራ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት የመንደር ፖለቲካ ነው" ሲሉት፤ ጠቅላላ የጠ/ሚሩ እንቅስቃሴ <u>ተንኮል እና ሴራ የተሞላበት ነው</u> የሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ በኔም በአብዛኛው ወገን ነበር፡፡ ለዚህ ጥርጣሬ የሚያጠናክረው ደግሞ በዛላንበሳ ግንባር፣ በመረብ ግንባር፣ በፆሮና እና በሌሎች ብዙ ድንበሮች የሁለቱ አገራት /ኢትዮጵያ እና ኤርትራ/ ህዝቦች ለመገናኘት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ የነበረ ቢሆንም፣ የኤርትራ መንግስት ቀና ፍላጎት ስላልታከለበት ሊሳካ አልተኛለም ነበር፡፡ በተለይ በአንዳንዶቹ ፍሪዳዎች ተጥለው ህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ይደረጋል ተብሎ ሲጠበቅ በኤርትራ በኩል ፍቃድ ተከልክሎ ህዝቡ ሳይመጣ ሲቀር ምንም ተስፋ ሳይቆረጥ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም የሁለቱ መንግስታት ፍቃድ ሆኖ በአዲስ ዓመት 2011 ዓ.ም. በጋራ ለማሳለፍ ስምምነት ሲደረግ ህዝቡ በደስታ እና በጉጉት ነበር የጠበቀው፡፡ እዚህ ላይ ግንኙነቱ የቁጥር ገደብ ተጥሎበት ከሁለቱም ህዝቦች እያንዳንዳቸው አንድ ሺ አምስት መቶ /1000-1500/ ሰዎች ብቻ ስርዓት ባለው ተመዝግቦ መግብያ ካርድ ተሰጥቶ እንዲገናኙ የሚል ነበር፡፡ ነገር ግን የሁለቱ መሪዎች መምጣት ይጠባበቅ የነበረው በርካታ ህዝብ መሪዎቹ እንደተቀበለ ወድያውኑ ፕሮግራሙ ሳይጠብቅ የመገናኘት ጉጉቱ ልክ እሳተ ጎመራ እንደ ፈንድቶ የቁጥር

ገደቡ ጥሶ የህዝቡን ማዕበል የድንበሩን ግንብ በማፍረስ ድብልቅልቁን ሲያወጡት ሁለቱም መሪዎች መቼ እንደ ሄዱም አልታዩም፡፡ ምክንያቱ ህዝቡ በሩጫ ዳሱን ጥሎ ወደ ናፈቀው ህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እና መሳሳም መለቃቀስ ነበር የገባው፡፡

ይህን የሁለቱም ህዝቦች የሰላም ፍላጎት እንደ ትልቅ ዕድል Opportunity በመውሰድ እንዲሁም የኤርትራ መንግስት የሰላም ፍላጎት በስጋት Threat ዓይን በማየት፣ ዕድሉን ለመጠቀም እና ስጋቱን ለመቀነፍ በሚል አጭር የአንድ ቀን ደርሶ መልስ ጉዞ ወደ ኤርትራ በማድረጌ የታዘብኩትን ትንሽ ላካፍላቹሁ፡፡

ኤርትራ ስገባ የተደበላለቀ /የደስታም የቁጭትም/ ስሜት ነበር የተሰማኝ፡፡ ለኤርትራ መንግስት እና ለኤርትራ ህዝብ የነበረኝን አመለካከት የሚያጠናክር ሆኖ ሳገኘው ድርጅቴን ኢህአዴግ በማድነቅ የነበረኝን የትግል ወኔ እንዲጨምር ድርጅታዊ እምነቴ እንዲጠናከር አደረገልኝ፡፡ ምክንያቱ ኢህአዴግ በየመድረኩ ስለ ኤርትራ ህዝብና መንግስት ይተነትነው የነበረ ትንታኔ በተግባር ትክክል መሆኑ ስላረጋገጥኩ፡፡ ኢህአዴግ አባላቱ እና አመራሩ ላይ ነው ችግር ያለበት እንጂ ድርጅታዊ ፕሮግራም፣ ዓላማዎቹ እና እሴቶቹ እውነትም ዘመን ተሻጋሪ ናቸው ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ አይሳሳትም አሁንም ወርቅ የሆነ መስመር እንዳለን በተግባር አረጋገጥኩ፡፡ ምክንያቱ በአጋጣሚ ኤርትራ ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በፊት አውቃት ስለነበር፣ አሁን ሳያት በአጭር አገላለፅ የተሰማኝን ስሜት ልክ ማታ ስተኛ የተውኩትን ነገር፣ ጥዋት ተነስቼ ምንም ነገር ሳይቀየር እንደተውኩት የማገኘው አይነት ሆና ነው ያገኘኋት፡፡ ለማለት የፈለግኩት ኤርትራ ልክ ከ30 ዓመት በፊት የተውኳትን ሆና ሳገኛት ለካ እኛ በልማቱ እና በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስንጠመድ የኤርትራ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን 20 ዓመት ሙሉ ምሽግ ላይ ተኝተው ነበር ያሳለፉት አልኩኝ፡፡ ምን አለው ይህ አሁን የተፈጠረ የሰላም ግንኙነት ከ10 እና 15 ዓመት በፊት ተፈጥሮ ቢሆን ኑሮ፣ ሁለታችን ወንድማማች አገሮች የት በደረስን ነበር፣ ብየ የቁጭት ስሜት ተሰማኝ፡፡ አንድ ወቅት ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂን የተናገሩትን "ኢትዮጵያ 70 እና 80 ጊዜ ሰላም እያሉ በራችን አንኳኩተው እምቢ አልናቸው" የሚል ንግግራቸው ሳስታውስ፣ ትዕቢት ነው እዚህ ያደረሰን ብዬ ፀፀት ተሰማኝ፡፡ ለካ በግለሰቦች የሚልዮኖች ህዝቦች ዕጣፈንታ ይወሰናል አልኩኝ፡፡

ኤርትራ በማዕድን ሃብት የታደለች አገር፣ ሁለት ወደቦች ያላት አገር፣ የአውሮፓ ስልጣኔ ቀድማ የጀመረች አገር፣ ዴሞክራሲና ነፃ ምርጫ ከአፍሪካ ቀድማ የጀመረች አገር /በዘውዳዊ ስርዓት ጊዜ ለማለት ነው/፣ ስልጡን እና ለአገሩ መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆነ ህዝብ

ያላት አገር፣ መንግስቱን እና መሪዉን ያዘዘው ለመስራት የማያመነታ ህዝብ ያላት አገር፣ 20 እና 30 ዓመት በእንቅልፍ ያሳለፈች አገር ስትባል በሌላ በኩል ደግሞ ከኤርትራ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ የነበረች እና ባልተፈለገ የወንድማማቾች ጦርነት ተገዳ የገባች አገራችን በ17 ዓመት፣ ለማመን የሚያስቸግር ለውጥ ያስመዘገበች አገር ስትባል፣ በእውነትም ግለሰቦች የሚልዮኖች እጣፈንታ የመወሰኑ ዓቅም አላቸው፡፡ ወደድንም ጠላንም ባለፉት 27 ዓመታት በተጨባጭ የታየው ነገር የ100 ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ያለፈውን የ27 ዓመት ዕጣፈንታ በክቡር መሪያችን መለስ ዜናዊ ሲወሰን፣ የ6 ሚሊዮን የኤርትራ ህዝብ ያለፉት 27 ዓመት እጣፈንታ በፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ተወስኗል፡፡

ኤርትራ ጉብኝት ላይ ሆኜ የጠቅላይ ሚኒስትራችን ዶ/ር አብይ አሕመድ በአሜሪካ የተናገሩት 27 ዓመት የጨለማ እና የቆሻሻ ጊዜ ነበር ያሉትን ነገር ሳስታውስ፣ እንዴ ኢትዮጵያ ባለፉት 27 ዓመታት በጨለማ ጊዜ ነው የነበረችው ከተባለ፣ ኤርትራን የጎበኙ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ምን ሊሏት ነው? ብየ ራሴን ጠየቅኩ እና ራሴን መልስ ሰጠሁ፡ ፡ ለካ ጠ/ሚ ዶክተር አብይ አሕመድ ኤርትራን ሲጎበኙ ልክ እኔ እንደተሰማኝ ኤርትራ 27 ዓመት በጨለማ እና በምሽግ እንቅልፍ ላይ የነበረች እንደሆነ በአእምሯቸው በማድረግ ነበር መግለጫው የሰጡት አልኩኝ፡፡

አሁን ያለፈ አልፏል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት አሁንም ማንም መስካሪ የማያስፈልገው ከዜጎችዋ ንቃተ ህሊና፣ ከአገሪቱ መሰረተ ልማት፣ ከገጠሩ ልማት፣ ከህዝቡ አኗኗር በማየት መናገር ቢቻልም ባለፉት 27 ዓመታት በተለይ ደግሞ ከኤርትራ ጦርነት ማብቅያ ጀምሮ የነበሩት 17 ዓመታት ሲታይ በተለይ ኤርትራን ካየሁ ቦኋላ ኢትዮጵያ በጨለማና በእንቅልፍ ላይ ሳይሆን የነበረች፣ ያለ እንቅልፍ ጨለማውን እንደ ብርሃን ስትጠቀምበት ነው የነበረችው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡

ነገር ግን የሁለቱም አገሮች ግንኙነት በተመለከተ ካየነው እውነትም 17 ዓመት የጨለማ እና የቆሻሻ ጊዜ ነበር፡፡

- ሁለቱም ህዝቦች ተነፋፍቀው ሲለቃቀሱ ስታይ፣
- ለ17 ዓመት ተዘግቶና ተበላሽቶ ውጥንቅጡ የወጣው ለመኪና የማይመች መንገድ 24 ሰዓት በመኪኖች ተጨናንቆ የመኪናው ደህንነት ሳይጨነቅ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ጥማት የሚጨነቅ ህዝብ ስታይ፣

- ድንበሩ በቅርብ ይዘጋል የተባለ እስኪመስል በተለይ መቐለን ጨምሮ የትግራይ የነጋዴዎች የንግድ መጋዝኖች ባዶ እስኪቀሩ ድረስ በመኪኖች ተጭነው ሲጓጓዙ ስታይ፤
- በመቐለ፣ ውቕሮ፣ አዲግራት፣ ዛላንበሳ፣ በሁሉም ዋናው መንገድ ላይ የሚገኙ ከተሞች የሚገኝ ህዝብ የኤርትራን እንግዶቹ ሲመጡ በልባዊ ፍቅር ሲቀበላቸው፣ ሲጋብዛቸው እና የስጋ ዝምድና የሌላቸው ነገርግን የተነፋፈቁ የአንድ እናት እና ኣባት ልጅ እስኪ መስሉ ድረስ ተነፋፍቀው አፍ-ለአፍ ተገናኝተው ሲያወሩ ስታይ፣
- በሁለቱ አገሮች ድንበር ላይ ያለው የተፈጥሮ ሃብት በጋራ ማልማት ሲቻል እና ሳይለማ መክኖ በጣም ብዙ ነገሮች ስታይ፤

እውነትም ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብዪ አህመድ እንዳሉት ያለፉት 17 ዓመታት የኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት የጨለማ ጊዜና የቆሻሻ ጊዜ ቢባል ያንሰዋል እንጂ ማጋነን አይሆንም፡፡

ስለዚህ በሁለቱ ህዝቦች የነበረውን ያለፈውን የጨለማ ጊዜ ዳግም እንዳይመለስ፤ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ሁለቱም ህዝቦች እርስ በርሳቸው ለመገናኘት እንደከፈሉት ከፍተኛ መስዋእትነት፣ አሁንም ሰላሙ ወደፊት እንዲራመድ ከፍተኛ ትንቅንቅ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይቅር እና አንድ አይነት ቋንቋ፣ ባህልና ወግ ያላቸው በጋብቻ በዝምድና የተሳሰሩ፤ በጋራ የጋራ ጠላት በማስወገድ መስዋእት የከፈሉና አንድ ጉድጓድ ላይ የተቀበሩ፣ ለዘመናት አብረው የኖሩ የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ህዝቦች፤ እንደዚህ ትስስር የሌላቸው ጎረቤታሞች የሆኑ አገሮችም ቢሆን አንዱን ሲለማ ሌላው ካልለማ የዛኛውም ልማት ልማት አይባልም፡፡ አብሮ መልማት እየተቻለ በምንቀኝነት በጥላቻ በቂም በቀል ህዝብንና አገርን መጉዳት ማንም ይቅር የማይለው ከፍተኛ ጉዳት እና ፀረህዝብነት መሆኑን በመገንዘብ አሁን ለተፈጠረው ሰላም ሁለቱም ህዝቦች ዘብ መቆም አለባቸው ለማለት እወዳለሁ፡፡

ህዳሴ ኢትዮጵያ

መስከረም 7፣ 2011 ዓ.ም.